፪/ ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

፫. **<u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>**

በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

፬. **<u>ስለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ኃላፊነት</u>**

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን የግብይት ሥርዓቱን ደህንነት ለማረጋገጥ በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፶፩/፲፱፻፺፱ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የድርጅቱን አሠራር ይቆጣጠራል፡፡

፭. **<u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>**

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፮. **<u>ዓላማ</u>**

የድርጅቱ ዓላማ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት ለሚካሄድባቸው የግብርና ምርቶች የመጋዘን አገልግሎት መስጠት ሲሆን በተለይ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ ስትራቴጂያዊ በሆኑ የአገሪቱ አካባቢዎች ዘመናዊ እና በቴክኖሎጂ የተደገፉ የምርት ማከማቻ መጋዘኖች መገንባትና ማስተዳደር፤

፪/ ምርቶችን በመቀበል ደረጃ ሰጥቶና መዝኖ በመጋዘን ሥርዓት ማከማቸት፣ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ መስጠት እና ምርትን ማስረከብ፤ እንዲሁም ዘመናዊ የሆነ የንብረት አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ፤

፫/ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወጡትን ደረጃዎች መሠረት በማድረግ የምርቶችን የጥራት ደረጃ የመወሰን ሥራ ማከናወን፤

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No.25/1992.

3/ **<u>Supervising Authority</u>**

A body to be designated by the government shall be the supervising authority of the Enterprise.

4. **<u>Responsibility of the Ethiopia Commodity Exchange Authority</u>**

The Ethiopia Commodity Exchange Authority shall regulate the activities of the Enterprise to ensure the integrity of all transactions in accordance with the powers provided under its establishment Proclamation No. 551/2007.

5. **<u>Head Office</u>**

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

6. **<u>Purposes</u>**

The purpose of the Enterprise is to render warehousing services for agricultural commodities traded in Ethiopia Commodity Exchange and shall have in particular the following purposes:

1/ to construct modern and technology based commodity warehouses in strategic locations of the country and manage same;

2/ to receive, grade, weigh, and deposit incoming commodities and deliver out-turn commodities; issue warehouse receipt and deliver commodity; put in place modern inventory management system and implement same;

3/ to carryout quality certification of commodities as per the grades and standards of the Ethiopia Commodity Exchange;

፬/ በኤሌክትሮኒክ የተደገፈ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና የተማከለ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥርዓት መዘርጋትና ማስተዳደር፤

፭/ በተገቢ የምርት ጥራት ቁጥጥር የሚመራ እና በምርት ደረጃ ላይ የተመሠረተ የክምችት ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፤

፮/ ለመረጃ አመዘጋገብ፣ ለቁጥጥር፣ ለመረጃ መለዋወጫ፣ ለሪፖርት ማስተላለፊያ የሚያገለግል እና ከተለያዩ የሥራ ማከናወኛ ጣቢያዎች ጋር የተያያዘ ደህንነቱ የተጠበቀ የኤሌክትሮኒክ የመረጃ መለዋወጫ ሥርዓትን መዘርጋትና መጠቀም፤

፯/ የተረከባቸውን፣ ያስረከባቸውንና በመጋዘን የቀሩትን ምርቶች በመጠን፣ በዓይነት እና በደረጃ በመለየት የየእለቱን ሁኔታ የሚያሳይ መረጃን ጨምሮ በማንኛውም ጊዜ የተሟላ መረጃ መያዝና ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ማስቀመጥ፤

፰/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያ ማስከፈል፤

፱/ የጥራት ደረጃን አስመልክቶ የሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና ውሳኔ የሚያገኙበት የቅሬታ መፍቻ ሥርዓት እና የአደጋ መከላከያ አስተዳደር ሥርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ፤

፲. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማከናወን።

## ፯. ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፩ ቢሊዮን (አንድ ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፪፻፶ ሚሊዮን (ሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት ተከፍሏል።



4/ to set up modern, efficient, centralized and automated warehouse receipt system and implement same;

5/ to put in place standardized grade- specific commodity depositing system with proper quality control regime;

6/ to put in place and utilize secured electronic communication system along with various working-stations that permits recording, monitoring, transmitting and reporting of data;

7/ to keep and maintain in a safe place complete records at all times, including daily position records showing the quantity, kind and grade of commodities received, delivered and the amount remaining in storage at the closes of each business day;

8/ to charge fees for its services;

9/ to provide complaint handling mechanism for resolution of grievances related to quality grading and put in place risk management system;

10/ to engage in any other related activities necessary for the attainment of its purposes.

## 7. Capital

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 1,000,000,000.00 (One Billion Birr) of which Birr 250,000,000.00 (Two Hundred Fifty Million Birr) is paid up in cash and in kind.

**፰. ኃላፊነት**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም::

**፱. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል::

**፲. መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ**

በአዋጅ ቁጥር ፭፻፶/፲፱፻፺፱ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከመጋዘን አገልግሎት ጋር የተያያዙ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል::

**፲፩. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

በዚህ ደንብ መሠረት ድርጅቱ በሙሉ አቅሙ አገልግሎት መስጠት እስኪችል የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከመጋዘን አገልግሎት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ዙሪያ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል::

**፲፪. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ጥር ፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**8. Liability**

The Enterprise may not be liable beyond its total assets.

**9. Duration**

The Enterprise is established for an indefinite duration.

**10. Transfer of Rights and Obligations**

The rights and obligations of the Ethiopia Commodity Exchange established under Proclamation No. 550/2007 relating to warehouse operations are hereby transferred to the Enterprise.

**11. Transitory Provisions**

As per this Regulation, the Ethiopian Commodity Exchange shall give necessary assistance to the Enterprise relating to warehousing services until the Enterprise operates to its full capacity.

**12. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 14th day of January, 2015.

HAILEMARIAM DESSALEGN

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA